የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No. 48
ADDIS ABABA, 30th July, 2026

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፬/፪ሺ፲፰

የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ……....................................ገጽ ፲፱ሺ፱፻፳፮

**Content**

Proclamation No. 1434/2026

Tax Administration Proclamation (Amendment) Proclamation………………………Page 19926

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፬/፪ሺ፲፰**

**የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፫/፪ሺ፰ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

በታክስ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የግብር ከፋዩን መብትና ግዴታ ሚዛናዊ በሆነ መልኩ በማስከበር፣ በአሠራር ላይ ቅልጥፍናን፣ ፍትሐዊነትን እና ታክስ የመክፈል ግዴታን በተጠናከረ ሁኔታ ተፈጻሚ ማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዘመናዊ የታክስ ስርአቶች ውስጥ መስማማትን ጨምሮ ሌሎች አማራጭ የአለመግባባት መፍቻ ዘዴዎች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ያለውን የታክስ አለመግባባቶችን የመፍቻ ሥርዓት ቅቡልነትና ውጤታማነት ለማሳደግ፣ አሠራሩን ከዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችና መርሆዎች ጋር ማጣጣምና ወጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

**PROCLAMATION NO.1434/2026**

**A PROCLAMATION TO AMEND THE TAX ADMINISTRATION PROCLAMATION NO. 983/2016**

**WHEREAS**, it has become necessary to foster the country's economic growth by ensuring a balanced enforcement of the rights and obligations of taxpayers within the tax administration system, thereby strengthening operational efficiency, equity, and compliance with tax obligations;

**WHEREAS**, modern tax systems increasingly utilize conciliation and other alternative dispute resolution mechanisms;

**WHEREAS,** it has become necessary to harmonize and render the tax dispute resolution system in Ethiopia consistent with international best practices and principles, with a view to enhancing its acceptability and efficacy;

በሀገር ውስጥ እየታየ ካለው ተለዋዋጭ እና በፈጣን ዕድገት ላይ ከሚገኘው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ጋር የታክስ አስተዳደር ሕግ ማዕቀፎችን የተጣጣሙና ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ያገናዘቡ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፬/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ማሻሻያ</u>**

የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፫/፪ሺ፰ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

፩) የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፊደልተራ (ሀ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፊደልተራ (ሀ) ተተክቷል፡-

፬/ (ሀ) የገቢዎች ሚኒስቴር።

፪) ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፵፭) ቀጥሎ የሚከተሉት ንዑስ አንቀጽ (፵፮)፣ (፵፯)፣ (፵፰) እና (፵፱) ተጨምረዋል፡-

፵፮/ **"መስማማት"** ማለት ለታክስ አለመግባባት የጋራ ተቀባይነት ያለው መፍትሔ መፈለግን አላማው ያደረገ ገለልተኛ በሆነ ሶስተኛ ወገን አመቻችነት እና ሙያዊ አስተያየት ሰጪነት የሚመራ በታክስ ከፋዩ እና በታክስ ባለስልጣኑ መካከል የሚደረግ ውይይት ሲሆን፤ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እና ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ አማራጭ አለመግባባትን የመፍቻ ስርዓት ነው፤

**WHEREAS**, it has become necessary to adapt the tax administration legal frameworks to align with and take into account the dynamic and rapidly growing domestic economic activities;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Tax Administration Proclamation (Amendment) Proclamation No. 1434/2026."

**2. <u>Amendment</u>**

The Tax Administration Proclamation No. 983/2016 is amended as follows:

1) Sub-Article (4) paragraph (a) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the Following new Sub-Article (4) paragraph (a) :

4/ (a) Ministry of Revenue.

2) The following new Sub Articles (46), (47), (48), and (49) are added after Sub Article (45) of Article 2 of the Proclamation:

46/ "**Conciliation**" means to a voluntary and confidential alternative dispute resolution mechanism comprising a structured dialogue between the taxpayer and the tax Authority, led by an independent third-party facilitator providing advisory opinions, aimed at finding a mutually acceptable solution to a tax dispute;

፵፯/ **"አስማሚ"** ማለት የታክስ ያለመግባባቶችን በመስማማት የመፍታትን ሂደት እንዲያመቻች በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የሚመረጥ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ ሰው ሲሆን፣ አስገዳጅ የሆነ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አይኖረውም፤

፵፰/ **"የታክስ ማጭበርበር"** ማለት ታክስን ለመሰወር ወይም ህጋዊ ያልሆነ የታክስ ጥቅም ለማግኘት ሲባል የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም ነው፡-

ሀ) ሐሰተኛ የሂሳብ መዝገቦችን፣ ሰነዶችን፣ ደረሰኞችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን ማቅረብ፤

ለ) ገቢን፣ ግብይትን ወይም ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ መደበቅ፤

ሐ) ሐሰተኛ ደረሰኞችን ማዘጋጀት ወይም መጠቀም፤

መ) ሐሰተኛ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ፣

ሠ) ሰነዶችን ማጥፋት፣ መቀየር ወይም መደበቅ፤

ረ) ከአንድ በላይ ወይም ትይዩ የሂሳብ መዛግብትን ወይም ሰነዶችን ማዘጋጀትና መያዝ፣ እንዲሁም ለታክስ ባለሥልጣኑና ለሌሎች አካላት ማቅረብ፤

ሰ) ሐሰተኛ የተቀናሽ ወጪዎችን፣ የግብር ወይም የታክስ ነፃ መብት፣ የተመላሽን ወይም የማካካሻ ጥያቄን ማቅረብ፤

ሸ) ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የታክስ ግዴታን ለመቀነስ ማናቸውንም ሌሎች ድርጊቶች መፈጸም ወይም ሕግ እንዲፈጸሙ የሚያስገድዳቸውን አለመፈጸም፡፡

47/ "**Conciliator**" means an independent and impartial person appointed by Office of the Prime Minister to facilitate the resolution of a tax dispute through conciliation, who shall have no power to render a binding decision;

48/ **"Tax Fraud"** means committing the following acts for the purpose of evading tax or obtaining an unlawful tax advantage:

a) submitting false books of account, documents, invoices or other tax documents;

b) concealing income ; transactions or taxable activities ;

c) issuing or using false or fictitious invoices or receipts;

d) filing a false tax returns;

e) destroying documents; altering or concealing records;

f) preparing and maintaining multiple or parallel accounting records or documents, as well as presenting them to the tax authority and other bodies;

g) claiming false deductions, tax exemptions, refunds or tax credits;

h) Committing any other act or omitting what is required by the law unlawfully reduce a tax liability.

፵፱/ **"አዲስ ማስረጃ"** ማለት የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው በኋላ በታክስ ከፋዩ የሚቀርብ አዲስ ሰነድ፣ መረጃ፣ ማስረጃ፣ ፍሬ ነገር ሲሆን፦

ሀ) በመጀመሪያው የታክስ አወሳሰን ሂደት ለታክስ ባለስልጣኑ ያልቀረበ፣

ለ) ለታክስ ውሳኔ ማስታወቂያው ትክክለኛነት አግባብነት ያለው እና መሰረታዊ የሆነ፣ እና

ሐ) በተወሰነው የታክስ መጠን ወይም በታክስ ከፋዩ ግዴታ ላይ መሰረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ነው፡፡

፫) ከአዋጁ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፲፫) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፬)፣ (፲፭) እና (፲፮) ተጨምረዋል፦

፲፬/ የታክስ ከፋዮች ምዝገባ የሚከናወነው ኢትዮጵያ የተቀበለችውን የዓለም አቀፍ የኢንዱስትሪ ምደባ ደረጃ መሰረት በማድረግ ነው።

፲፭/ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋ እና ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት እና ታክሱን በአግባቡ ለመሰብሰብ እንዲቻል የታክስ ባለስልጣኑ የታክስ ከፋዮችን በተለያየ ምድብ ሊመድብ ይችላል፣ ዝርዝር አፈፃፀሙ የታክስ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፲፮/ ባለስልጣኑ ለታክስ ከፋዮች የሚሰጠውን የአገልግሎት ደረጃ፣ ጥራትና ቅልጥፍና በይፋ የሚያሳውቅበት የደንበኞች ቻርተር ያወጣል።

49/ "**New Evidence**" means any new document; information;evidence; or factual matter presented by the taxpayer after the receipt of a tax assessment notice, which:

a) was not previously submitted to the Tax Authoritys;

b) is relevant and material to the accuracy of the tax assessment notice; and

c) is capable of materially modifying the assessed tax amount or the tax liability of the taxpayer.

3) The following new Sub Articles (14), (15) and (16) are added after Sub Article (13) of Article 9 of the Proclamation:

14/ Taxpayer registration shall be conducted based on the International Standard for Industry Classification approved by Ethiopia.

15/ The Tax Authority may segment taxpayers in different categories for the purpose of rendering fair; efficient and effective services. The details shall be determined in a Directive to be issued by the Tax Authority.

16/ The Authority shall issue a citizens' charter publicly declaring the standard; quality and efficiency of services it provides to taxpayers.

፬) የአዋጁ አንቀጽ ፳፰ ርዕስ በሚከተለው አዲስ ርዕስ ተሻሽሎ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፡

**፳፰. <u>የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች እና የይርጋ ጊዜ ገደብ</u>**

፪/ አግባብነት ባለው የታክስ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር፣ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ማንኛውንም የታክስ ስሌት፡-

ሀ) የታክስ ባለስልጣኑ የታክስ ማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያገኘ እንደሆነ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያውን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፲ (አስር) ዓመት ውስጥ፤ ወይም

ለ) በሌላ በማናቸውም ሁኔታ በሚከተለው የይርጋ ጊዜ ውስጥ፡ -

(፩) ታክስ ከፋዩ በራሱ የሚያሰላው የታክስ ስሌት ሲሆን ታክስ ከፋዩ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያውን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፭ (አምስት) ዓመት ውስጥ፤

(፪) ለሌላ ማንኛውም የታክስ ስሌት ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፭ (አምስት) ዓመት ውስጥ

ሊያሻሽል ይችላል፡፡

4) The title of Article 28 of the Proclamation is replaced by the following new title and Article 28 Sub Article (2) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub Article (2):

**28. <u>Amended Assessment and Period of Limitation</u>**

2/ unless otherwise provided for in the relevant tax law, the Authority may amend tax assessment pursuant to Sub Article (1) of this Article:

a) Where the Tax Authority obtains evidence proving that the taxpayer has committed Tax Fraud, within 10 (Ten) years from the date the taxpayer filed the self-assessment notice; or

b) in any other case, the following limitation periods:

(1) for self-assessment, within 5 (Five) years from the date the taxpayer filed the self-assessment notice;

(2) for any other assessment, within 5 (Five) years from the date the Tax Authority issued the tax assessment notice to the taxpayer.

፭) ከአዋጁ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሮ ነባሮቹ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና ንዑስ አንቀጽ (፮) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፮) እና (፯) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡-

፭/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም የታክስ ማጭበርበር ድርጊት መፈጸሙ በማስረጃ የተረጋገጠ በሚሆንበት ጊዜ የታክሱ ባለስልጣን የ ፲ (አስር) ዓመቱን የይርጋ ጊዜ ገደብ ሳያልፍ በማናቸውም ጊዜ የታክስ ውሳኔ ማሻሻያን ሊያደርግ ይችላል፡፡

፮) የአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተተክቷል፡-

፭/ የታክሱ ባለሥልጣን ለፋይናንስ ተቋሙ የዕግድ ትዕዛዝ በደረሰው በ፲ የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ትዕዛዙ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችል የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

፯) የአዋጁ አንቀጽ ፶፱ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፶፱ ተተክቷል፦

**፶፱. <u>የማስረዳት ኃላፊነት እና አዲስ ማስረጃ ማቅረብ</u>**

፩/ በዚህ ክፍል መሰረት ከታክስ ውሳኔ ጋር በተገናኘ በሚደረግ ማናቸውም የታክስ ክርክር ሂደት የታክስ ውሳኔ ትክክል ያለመሆኑን የማስረዳት ኃላፊነት የታክስ ከፋዩ ነው፡፡

5) A new Sub Article (5) is added after Sub Article (4) of Article 28 of the Proclamation, and the existing Sub Articles (5) and (6) are renumbered as Sub Articles (6) and (7) respectively:

5/ Notwithstanding the provisions of this Article, where it is proven by evidence that an act of fraud has been committed, the tax Authority may carry out a reassessment at any time within the ten year period of limitation.

6) Sub Article (5) of Article 42 of the Proclamation is hereby repealed and replaced by the following new Sub Article (5):

5/ The Authority shall, within 10 working days from the date of receipt of the freezing order by the financial institution, obtain a court authorization to enable the continuation of the order.

7) Article 59 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 59:

**59. <u>Burden of Proof and Presentation of New Evidence</u>**

1/ In any proceeding under this Part in relation to a tax decision, the burden shall be on the taxpayer to prove that the tax decision is incorrect.

፪/ በዚህ አዋጅ መሰረት ቅሬታ፣ ይግባኝ ወይም የውሳኔ ማስተካከያ ጥያቄን የሚያቀርብ ታክስ ከፋይ በታክስ ውሳኔ ወቅት ካቀረበው የተለየ አዲስ ማስረጃን ማቅረብ አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም አዲስ ማስረጃ በቅሬታ፣ ይግባኝ ወይም ስህተትን ለማረም በሚቀርብበት ወቅት ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው፦

ሀ/ የማስረጃው አለመታየት በታክስ ከፋዩ የታክስ እዳ ላይ ከፍተኛ ጫናን የሚያስከትል ከሆነ፤

ለ/ ታክስ ከፋዩ ማስረጃውን ያገኘው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው በኋላ ከሆነ፤ ወይም

ሐ/ ሰነዱ ያልቀረበው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ፤

ይሆናል::

፰) ከአዋጁ አንቀጽ ፷ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ከአንቀጽ ፷፩ እስከ ፸፩ ያሉት አንቀጾች ተጨምረው የአዋጁ ነባር አንቀጽ ፷፩ እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አንቀጽ ፸፪ እና ተከታዮቹ ሆነው ተሸጋሽገዋል፦

**፷፩. <u>የታክሱ ባለስልጣን የታክስ አለመግባባትን በመስማማት ለመፍታት ያለው ስልጣን</u>**

፩/ የታክሱ ባለስልጣን የታክስ አለመግባባቶችን በመስማማት የመፍታት ስልጣን ተሰጥቶታል።

፪/ ማናቸውም በስምምነት የሚፈታ የታክስ አለመግባባት በጽሁፍ የሚደረግ እና የተስማሚ ወገኖች ፊርማ ያረፈበት ሊሆን ይገባል፡፡

2/ A taxpayer who submits an objection, an appeal, or a request for correction of an error under this Proclamation shall not present any new evidence that is different from the evidence presented during the initial tax assessment.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, new evidence may be admissible during an objection, an appeal, or a request for correction of error only where:

a) The non-consideration of the evidence would cause a heavy tax liability on the taxpayer;

b) The taxpayer obtained the new evidence after the tax assessment notice was issued; or

c) the taxpayer was unable to submit the new evidence due to force majeure.

8) The following new Articles 61 to 71 are added after Article 60 of the Proclamation and the existing Article 61 and the following provisions of the Proclamation are renumbered as Articles 72 and the following:

**61. <u>Power of the Authority to Settle Disputes through Conciliation</u>**

1/ The Authority may settle a tax dispute through conciliation.

2/ Any tax dispute resolved through conciliation shall be in writing and signed by the contracting parties.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲኖሩ ጉዳዩ በማስማማት ሊታይ አይችልም፦

ሀ) የታክስ ማጭበርበር ወይም ሆን ተብሎ የተደረገ ታክስን የመሰወር ድርጊት ወይም ሌላ ከታክስ ጋር የተገናኘ ወንጀል መኖሩ ሲጠረጠር፤

ለ) በመስማማት የሚደረግ ስምምነት ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት እና ከሚመለከታቸው የታክስ ሕጎች ጋር የሚጋጭ ሲሆን፤

ሐ) ከሁለቱ ወገኖች አንዱ በሽምግልና ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ካልሆነ፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ የአስማሚውን የትምህርት እና ሙያ ደረጃን ጨምሮ የመስማማት ሂደት የሚመራበትን ሥርዓት የሚወስን ዝርዝር የአፈጻፀም መመሪያ ያወጣል፡፡

፷፪. <u>የታክስ አለመግባባትን ለመስማማት ስለመምራት</u>

፩/ የታክስ አለመግባባት ለመስማማት ሊመራ የሚችለው በታክሱ ባላስልጣን እና በታክስ ከፋዩ መካከል የታክስ አለመግባባቱን በማስማማት ለመፍታት ስምምነት ሲደረስ ነው፡፡

፪/ የታክስ አለመግባባት በመስማማት እንዲፈታ የሚደረገው በአዋጁ መሰረት ቅሬታ ከቀረበ በኋላ ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ውሳኔ ላይ ብቻ ነው፡፡

3/ Notwithstanding the provisions of Sub Article (1) of this Article, no settlement through conciliation shall be allowed on the following conditions:

a) when fraud or intentional tax evasion or other tax related crime was suspected to be committed;

b) when settlement through conciliation is contrary to the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and relevant tax laws;

c) when one of the parties to the conciliation has not given its consent.

4/ The Ministry shall issue a detailed implementation Directive determining the code of procedure for conducting the conciliation process, including the educational and professional qualifications of the conciliator.

**62. <u>Referral of Disputes to Conciliation</u>**

1/ A tax dispute may be referred to conciliation by agreement of the Tax Authority and the Tax payer.

2/ A tax dispute may be resolved through conciliation only after an objection has been lodged pursuant to the Proclamation and only in respect of an appelable decision.

፫/ ይግባኝ ያቀረበ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ይግባኙን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፴ ቀናት ውስጥ፣ ክርክሩ በመስማማት እንዲፈታ በተወሰነው ቅጽ መሰረት የጽሑፍ ጥያቄ ለታክሱ ባለስልጣን ማቅረብ ይችላል፤

፬/ የታክስ እርግጠኝነትንና ቀልጣፋ አሰራርን የሚያረጋግጥ ሆኖ ሲገኝ፣ ባለሥልጣኑ በታክስ ከፋዩ ስምምነት በማንኛውም የይግባኝ ክርክር ሂደት ላይ ጉዳዩን ወደ መስማማት ሊመራው ይችላል።

፭/ የታክስ አለመግባባት ወደ መስማማት እንዲመራ መደረጉ ለአቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት ከሚቀርብ ማመልከቻ በስተቀር ሌሎች በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የታክስ አለመግባባት መፍቻ ዘዴዎችን መጠቀምን የሚከለክል አይሆንም።

**፷፫. <u>የታክስ አለመግባባት በመስማማት እንዲፈታ ስለሚቀርብ ጥያቄ</u>**

፩/ የታክስ አለመግባባት በመስማማት እንዲፈታ የሚፈልግ ታክስ ከፋይ ይህንኑ በመግለጽ ለታክስ ባለስልጣኑ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል።

፪/ የታክሱ ባለስልጣን የታክስ አለመግባባቱ በመስማማት ሊፈታ የሚችል መሆን ያለመሆኑን ይወስናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የስምምነት ጥያቄ ማቅረብ ታክስ ከፋዩ በባለሥልጣኑ የተወሰነውን እና አከራካሪ ያልሆነውን የታክስ መጠን የመክፈል ግዴታን አያስቀርም።

3/ Any taxpayer who has filed an appeal may within 30 days from the date of filing the appeal, submit a written request in the prescribed form for the dispute to be resolved through conciliation;

4/ Where it ensures tax certainty and administrative efficiency, the Authority may with the consent of the taxpayer refer the matter to conciliation at any stage of the appeal proceedings.

5/ The referral of a tax dispute to conciliation shall not preclude the utilization of other tax dispute resolution mechanisms provided under this Proclamation, except for an application submitted to the Complaint Review Office.

**63. <u>Application for Conciliation</u>**

1/ A taxpayer who desires to resolve a tax dispute through conciliation may submit an application to the tax Authority to that effect.

2/ The tax Authority shall determine whether or not the tax dispute is eligible to be resolved through conciliation.

3/ Submitting a request for conciliation pursuant to this Article shall not discharge the taxpayer from the obligation to pay the undisputed tax amount assessed by the Authority.

Habtamu Hailemeskel-Attorney & Legal Consultant

## ፷፬. <u>የሌሎች ሂደቶች መታገድ</u>

፩/ የታክስ አለመግባባቱ በመስማማት በሚታይበት ጊዜ፣ በአዋጁ አንቀጽ ፹፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና አንቀጽ ፺፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተቀመጡት የጊዜ ገደቦች ተፈጻሚነት ታግዶ ይቆያል፡፡

፪/ የመስማማቱ ተሳታፊ ወገኖች የታክስ አለመግባባቱን በመስማማት ለመፍታት ካልቻሉ፣ የማስማማቱ ሂደት ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ በአዋጁ የተቀመጡት የጊዜ ገደቦች ተፈጻሚነት ይቀጥላል፡፡

## ፷፭. <u>አስማሚ ስለመመደብ</u>

፩/ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ነፃ እና ገለልተኛ የሆነ አስማሚ ይመድባል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚመደበው አስማሚ ገለልተኛ እና የሙያ ብቃት ያለው መሆን አለበት፡፡

## ፷፮. <u>የአስማሚው ሚና</u>

፩/ አስማሚው ተከራካሪ ወገኖች ለክርክሩ ፍትሐዊ መፍትሄ እንዲያገኙ ለመርዳት ገለልተኛ እና አድልዎ የማያደርግ ባለሙያ ሆኖ ይሠራል፡፡

፪/ ሂደቱን በሚመራበት ጊዜ አስማሚው የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፦

ሀ) ተከራካሪ ወገኖች አከራካሪ በሆኑ ነጥቦች ላይ የጽሑፍ መግለጫዎችን እና ደጋፊ ማስረጃዎችን እንዲያቀርቡ መጠየቅ፤

## 64. <u>Suspension of Other Proceedings</u>

1/ Where a tax dispute is reviewed through conciliation, the running of the limitation periods provided under Article 88 Sub-Article (1) and Article 91 Sub-Article (2) of the Proclamation shall be suspended.

2/ Where the participants of the conciliation fail to resolve the tax dispute through conciliation, the running of the limitation periods provided under the Proclamation shall resume from the date the conciliation process is concluded.

## 65. <u>Appointment of Conciliator</u>

1/ Office of the Prime Minister shall appoint an independent and impartial Conciliator.

2/ The Conciliator appointed in accordance with Sub Article (1) of this Article shall be impartial and qualified.

## 66. <u>The Role and Functions of Conciliator</u>

1/ The conciliator shall act as an independent and impartial professional to assist the disputing parties in reaching a fair resolution to the dispute.

2/ In conducting the proceedings, the conciliator shall have the following powers:

a) to request the disputing parties to submit written statements and supporting evidence on the disputed issues;

ለ) የታክስ ያለመግባባት በስምምነት እንዲፈታ ለማድረግ የታክስ ባለስልጣኑ እና ታክስ ከፋዩ ላለመግባባቱ መነሻ የሆኑትን የፍሬነገር፤ የህግ፤የቴክኒክ እና የማስረጃ ጭብጦችን በሚገባ እንዲመረምሩ እገዛ ማድረግ፤

ሐ/ በማንኛውም የማስማማት ሂደቱ ደረጃ ላይ ወገኖች እንዲመክሩበት የዕርቅ ስምምነት ነጥቦችን የያዘ ምክረ ሀሳብ ማርቀቅ እና ማቅረብ፤

መ/ ተከራካሪ ወገኖች ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ጉዳዩ ወደ ይግባኝ ሰሚ ወይም ወደ ፍርድ ቤት ቢቀጥል ሊኖረው የሚችለውን ውጤት በተመለከተ አስገዳጅ ያልሆነ የሙያዊ አስተያየት መስጠት፡፡

፷፯. <u>የመስማማት አካሄድ</u>

፩/ የመስማማት ሂደት የሚመራው በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፦

ሀ) የማስማማቱ ሂደት ገለልተኝነትን እና ሚስጥራዊነትን መሰረት ባደረገ አኳኋን መካሄድ አለበት፤

ለ) የአስማሚው የስራ ድርሻ የማስማማት ሂደቱን የማመቻቸት እና የውሳኔ ሐሳብ የማቅረብ እንጂ ውሳኔ መስጠት አይሆንም፤

ሐ) የማስማማቱ ሂደት መደበኛ የሆኑ የስነ ስርዓት ደንቦችን ላይከተል ይችላል፡፡

b) for purposes of facilitating amicable settlement to assist the tax Authority and the taxpayer in thoroughly examining the factual; legal; technical and evidentiary issues underlying the dispute;

c) To draft and present proposal containing terms of settlement at any stage of the conciliation process for the consideration of the parties;

d) To render a non-binding professional opinion regarding the potential outcome should the matter proceed to an appellate body or a court of law, in the event that the disputing parties fail to reach an agreement.

**67. <u>Conduct of Conciliation</u>**

1/ the Conciliation process shall be conducted in the following manner:

a) shall be conducted based on neutrality and confidentiality;

b) The Conciliator’s role shall be to facilitate the process but does not decide;

c) The conciliation process may not apply formal procedures .

፪/ የታክስ አለመግባባትን በመስማማት ለመፍታት ስምምነት ከተደረሰበት ቀን ጀምሮ በ፷ ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የስምምነት ሂደቱ ከ ፷ ቀናት በላይ ሊራዘምበት የሚችልበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፷፰. **ሚስጥራዊነት**

፩/ ማናቸውም በማስማማቱ ሂደት የሚደረግ ግንኙነት በሚስጥር መጠበቅ አለበት፡፡

፪/ በህግ መሰረት ወይም በተሳታፊ ወገኖች ስምምነት ካልሆነ በስተቀር የማስማማቱ ውጤት በማናቸውም የይግባኝ መድረክ በማስረጃነት ሊያገለግል አይችልም፡፡

፷፱. **ስምምነት**

፩/ ተሳታፊ ወገኖች በማስማማቱ ውጤት ከተስማሙ ስምምነቱ፦

ሀ) በጽሑፍ መደረግ ያለበት ሲሆን፤ ተሳታፊ ወገኖች ሊፈርሙበት ይገባል፤

ለ) አስገዳጅ እና ተፈጻሚነት ያለው ይሆናል፡፡

፪/ የታክሱ ባለስልጣን የመስማማት ስምምነቱን ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚደረስ ማንኛውም ስምምነት ለክርክሩ መነሻ በሆነው ታክስ ከፋይ እና የግብር ዘመን (ዘመናት) ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2/ Conciliation shall be completed within 60 days from the date the parties have agreed to settle the tax dispute through Conciliation.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the conditions under which the conciliation process may be extended beyond 60 days shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry.

68. **Confidentiality**

1/ All communications during the process of conciliation shall be kept confidential.

2/ The Conciliation result shall not serve as evidence in any appeal process except as provided by law or the consent of the Parties.

69. **Conciliation Agreement**

1/ If the parties agree on the conciliation result the agreement shall be:

a) made in writing and signed by both parties;

b) binding and enforceable on both parties.

2/ The Authority shall implement the Conciliation agreement.

3/ Any agreement reached pursuant to this Article shall apply only to the specific taxpayer and the tax period ( periods) underlying the dispute.

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረግ የፍሬ-ነገር ወይም የሕግ ክርክሩ ተመሳሳይ ቢሆንም እንኳ በሌላ በማንኛውም ክርክር ወይም የግብር ዘመን ላይ በባለሥልጣኑ ወይም በሌላ ታክስ ከፋይ ላይ አስገዳጅነት አይኖረውም፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሰረት በታክስ ባለስልጣኑ እና በታክስ ከፋዩ መካከል ስምምነት የተደረሰው በከፊል ጉዳዮች ላይ ከሆነ፣ ስምምነቱ ተፈፃሚ የሚሆነው ስምምነት በተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ ይሆናል፡፡

**፸. ያለመስማማት**

የማስማማቱ ተሳታፊ ወገኖች በማስማማቱ ውጤት ካልተስማሙ፣ ታክስ ከፋዩ በአዋጁ አንቀጽ ፩፻፭ መሰረት ይግባኙን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም አግባብነት ላለው ፍርድ ቤት ለማቅረብ ይችላል፡፡

**፸፩. ወጪዎች**

፩/ እያንዳንዱ የማስማማቱ ተሳታፊ ለማስማማቱ የሚያስፈልገውን የራሱን ወጪ መሸፈን አለበት፡፡

፪/ ለአስማሚው የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ በታክስ ከፋዩ ይሸፈናል፡፡

፱) ከአዋጁ አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ (፭) ወይም በተሻጋሸገው አንቀጽ ፸፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮)እስከ (፲፩) ያሉት ድንጋጌዎች ተጨምረዋል፡-

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የታክሱ ባለስልጣን በሚከተሉት ምክንያቶች ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ላለበት ታክስ ከፋይ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የታክስ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል፦

4/ Notwithstanding that the factual or legal issues may be identical an agreement reached pursuant to this Article shall have no binding effect on any other dispute or tax period against the Authority or any other taxpayer.

5/ Where an agreement under this Article is reached between the tax Authority and the taxpayer only on partial matters, the agreement shall be applicable solely to the matters agreed upon.

**70. Failure of Conciliation**

Where the participants of the conciliation fail to agree on the outcome of the conciliation, the taxpayer may file an appeal to the Tax Appeal Commission or to the competent court of law pursuant to Article 105 of the Proclamation.

**71. Costs**

1/ Each participant of the conciliation shall bear their own costs incurred for the conciliation process.

2/ The service fee payable to the conciliator shall be covered by the taxpayer.

9) The following new Sub Articles (6) to (11) are added after Sub Article (5) of Article 61 or the renumbered after Sub Article (5) of Article 72 of the Proclamation:

6/ Notwithstanding Sub Article (2) of this Article, the Tax Authority may issue a conditional tax clearance certificate to a taxpayer who has outstanding tax liabilities due to the following reasons:

ሀ) ታክስ ከፋዩ በዚህ አዋጅ መሰረት ስልጣን ለተሰጠው አካል የታክስ መቃወሚያ አቤቱታ፣ ይግባኝ ወይም የታክስ ክርክር ያቀረበ ከሆነ፣

ለ) የሚፈለግበትን የታክስ እዳ ለመክፈል ከታክሱ ባለስልጣን ጋር የጸና የክፍያ ስምምነት የፈጸመ ከሆነ፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚሰጠው የታክስ የምስክር ወረቀት ለሚከተሉት ተግባራት የሚያገለግል ይሆናል፡-

ሀ) የንግድ ስራ ፈቃድ ወይም የሙያ ፈቃድ ለማደስ፣

ለ) በጨረታ ለመሳተፍ፣

ሐ) ለተሽከርካሪዎች ወይም የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ዓመታዊ ምዝገባና ምርመራ /ክላውዶ/ ለማድረግ፣ እና

መ) የባንክ ብድር ለማግኘት፡፡

፰/ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የታክስ የምስክር ወረቀት፡-

ሀ) የታክስ ከፋዩን ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚያስቀር፣ የሚያግድ ወይም ግዴታውን የተወጣ ሆኖ እንዲቆጠር የሚያስችል አይሆንም፣

ለ) የታክሱ ባለስልጣን ያልተከፈለውን ታክስ በማስከፈል ረገድ ያለውን መብት የሚያሳጣ አይሆንም፣

ሐ) በሂደት ላይ ያለውን የታክስ አለመግባባት ወይም ክርክር ውጤት የሚያስቀር አይሆንም፡፡

፱/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚሰጠው የታክስ የምስክር ወረቀት ተፈጻሚ የሚሆነው ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ለሚወስነው የጊዜ ገደብ ሲሆን በመመሪያው በሚዘረዘሩ ምክንያቶች ሊሻር ይችላል፡፡

a) The taxpayer has formally lodged an objection; appeal or tax dispute before the competent authority in accordance with this Proclamation;

b) the taxpayer has entered into a valid installment agreement with the Tax Authority on the settlement of the outstanding tax liability.

7/ A conditional tax clearance certificate issued under this Article serve the following purposes:

a) to renew business or professional license;

b) to participate in a bid;

c) for annual inspection of vehicles or construction machineries; and

d) to obtain bank loan.

8/ The issuance of a conditional tax clearance certificate shall not:

a) constitute a waiver, suspension or discharge of the taxpayer’s liability;

b) prejudice the rights of the Tax Authority to recover any tax due; or

c) affect the outcome of any pending dispute or proceeding.

9/ Tax clearance certificate issued under this Article shall be valid for such period as may be prescribed by a Directive to be issued by the Ministry and may be revoked for reasons mentioned in such Directive.

፲/ በአዋጁ አንቀጽ ፵ ንኡስ አንቀጽ (፯) ድንጋጌ መሰረት የተሰጠ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት በአዋጁ አንቀጽ ፴፫ (፩) በተዘረዘሩ የታክስ አይነቶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

፲፩/ ባንኮች የውጭ ባለሃብት ትርፉን፣ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻውን ወይም ድርጅቱን በመሸጥ ያገኘውን ገቢ ወደውጭ እንዲልክ ከማድረጋቸው በፊት በትርፉ ወይም በአክሲዮን ድርሻው ወይም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ግብር የከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ በታክስ ባለስልጣኑ የተሰጠ የታክስ የምስክር ወረቀት እንዲቀርብ መጠየቅ አለባቸው።

፲) ከአዋጁ አንቀጽ ፹፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፺፫ ንዑስ አንቀጽ (፭) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተጨምሯል፡-

፮/ የታክሱ ባለስልጣን የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ስርአትን፣ የፈጣን ምላሽ ኮድ የያዘን ደረሰኝ አጠቃቃምን፣ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለሚፈጸም ግብይት እና ለማናቸውም ሌላ ግብይት የሚሰጥን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ በሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፲፩) የአዋጁ አንቀጽ ፹፭ ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፺፮ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፺፮ ተተክቷል፡-

**፺፮. <u>የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያን ስለማስተካከል</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች የተደነገገው ቢኖርም፣ የታክሱ ባለስልጣን ለታክስ ከፋዩ የደረሰው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ስህተት ወይም ግድፈት ያለበት ሆኖ ካገኘው ስህተቱን ወይም ግድፈቱን ለማስተካከል በሚያስፈልግ መጠን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያውን ሊለውጥ ይችላል።

10/ The tax clearance certificate issued under Sub-Article (7) of Article 40 of this Proclamation shall not apply to taxes listed under Article 33 Sub-Article (1) of the Proclamation.

11/ Banks shall, prior to allowing a foreign investor to repatriate profits, dividends, or proceeds from the sale of a business, require the investor to present a tax clearance certificate issued by the tax Authority confirming that tax has been paid on such profits, dividends, or taxable transactions.

10) The following new Sub-Article (6) is added after Sub-Article (5) of Article 82, or renumbered after Sub-Article (5) of Article 93 of the Proclamation:

6/ The Tax Authority shall issue Directive on use of electronic tax system, invoice with Quick Response Code; e-commerce and any other taxable transaction to which electronic invoice is issued.

11) Article 85 or renumbered Article 96 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Articles 96፡

**96. <u>Power to Revise Assessment</u>**

1/ Notwithstanding any other provisions of this Proclamation, where the tax Authority finds that a tax assessment notice served on a taxpayer contains an error or omission it may amend the tax assessment notice to the extent necessary to rectify such error or omission.

፪/ የታክሱ ባለስልጣን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የሚስተካከልበትን አግባብ ሊኖር የሚገባውን የአሰራር ሂደት የሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፪) ከአዋጁ አንቀጽ ፹፭ ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፺፮ ቀጥሎ የሚከተሉት ከአንቀጽ ፺፯ እስከ ፩፻፪ ያሉ አዲስ ድንጋጌዎች ተካተዋል፦

**፺፯. <u>የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያን ለማስተካከል የሚያስችሉ ምክንያቶች</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፮ መሰረት በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ ማስተካከያ ሊደረግ የሚችለው፦

ሀ) የስሌት ወይም የሂሳብ ስህተት ያለ ከሆነ፤

ለ) በታክስ አወሳሰን ወቅት ያልታየ አግባብነት ያለው ማስረጃ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የቀረበ አዲስ ማስረጃ ያለ እንደሆነ፤

ሐ) የታክስ ውሳኔው አስገዳጅ ከሆነው የታክስ ህጎች ትርጉም ጋር የማይጣጣም ከሆነ፤ ወይም

መ) ታክስ የመክፈል ግዴታን በመወሰን ረገድ የተሳሳተ ውጤት የሚያስከትል ሌላ ስህተት ካለ ነው፡፡

**፺፰. <u>የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ለማስተካክል የሚያስችሉ ሁኔታዎች</u>**

የታክሱ ባለስልጣን በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ ማስተካከያ ሊያደርግ የሚችለው፦

ሀ) ስህተቱ መሰረታዊ ከሆነ እና ሊከፈል የሚገባውን ወይም ተመላሽ መደረግ ባለበት ታክስ መጠን ላይ ውጤት የሚኖረው ከሆነ፤

2/ The tax Authority may issue a Directive regarding the appropriate procedures for the amendment of a tax assessment notice.

12) The following new Articles 97 up to 102 are added after Article 85 or renumbered Article 96:

**97. <u>Grounds for Amending a Tax Assessment Notice</u>**

An amendment may be made to a tax assessment notice pursuant to Article 96 of this Proclamation only where:

a) there is a computational or arithmetical error;

b) There is relevant evidence that was not considered during the tax assessment or new evidence presented in accordance with this Proclamation**;**

c) the assessment is inconsistent with binding administrative rulings; or

d) any other mistake that results in an incorrect determination of tax liability.

**98. <u>Conditions for Revision of a Tax Assessment Notice</u>**

The Tax Authority shall revise an assessment only where:

a) the mistake is material and affects the amount of tax payable or refundable;

ለ) ማስተካከያው ሊረጋገጥ በሚችል መረጃ ወይም ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ከሆነ፤ወይም

ሐ) አዲስ ማስረጃ በመገኘቱ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ታክስ ከፋዩ ማስረጃውን ለማቅረብ ባለመቻሉ ካልሆነ በስተቀር፣ ታክስ ከፋዩ ስህተት እንዲታረምለት ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ጉዳዩ በይግባኝ ከመታየቱ በፊት ነው።

## ፺፱. የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻልበት ጊዜ

፩/ ስህተት የማረም ሂደት የሚጀመረው ታክስ ከፋዩ ስህተት ይታረምልኝ የሚል ማመልከቻ ሲያቀርብ ወይም የታክሱ ባለስልጣን በራሱ ተነሳሽነት ስህተት መኖሩን ሲያምንበት ነው፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፰ ፊደልተራ (ሐ) በተደነገገው መሰረት የታክሱ ባለልጣኑ በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ ማስተካከያ ማድረግ የሚችለው በሚከተለው ጊዜ ውስጥ ይሆናል፦

ሀ) የመጀመሪያው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ ፭ (አምስት)አመታት ውስጥ፤ ወይም

ለ) ስህተቱ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በ ፩ (አንድ) አመት ውስጥ፤ ከሁለቱ በቀደመው ጊዜ፡፡

b) the revision is based on verifiable information or evidence;

c) Except where new evidence is discovered or the taxpayer was unable to present the evidence due to force majeure, the taxpayer may submit a request for rectification of an error only before the matter is reviewed on appeal.

## 99. Time Limit for Revision of a Tax Assessment Notice

1/ The process of revision shall be initiated upon the submission of an application for rectification by the taxpayer or where the tax Authority on its own initiative, determines that an error exists;

2/ Pursuant to Article 98 paragraph (c) of this Proclamation, the tax Authority may amend a tax assessment notice within:

a) 5 (Five) years from the date the initial tax assessment notice was issued; or

b) 1 (One) year from the date the error was discovered; whichever period expires earlier.

**፩፻. የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ማስተካከያ የሚኖረው ውጤት**

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚዘጋጀው የተስተካከለ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ፦

ሀ) በተደረገው ማስተካከያ ልክ የመጀመሪያውን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የሚተካ ይሆናል፤

ለ) በዚህ አዋጅ መሰረት እንደተሰጠ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ይቆጠራል፡፡

፪/ ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የማስተካከያ ጥያቄ ተቀባይነት ያላገኘ ከሆነ፣ በዚህ አዋጅ ቅሬታ ለማቅረብ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ የመጀመሪያው የውሳኔ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር ይሆናል፡፡

**፻፩. የተስተካከለውን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ስለማስታወቅ**

የታክሱ ባለስልጣን የተስተካከለውን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በሚመለከት የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ መላክ አለበት፡-

ሀ) የስህተቱን አይነት፤

ለ) የማስተካከያውን ምክንያት፤

ሐ) በማስተካክያው ምክንያት ሊከፈል የሚገባውን ወይም ተመላሽ የሚደረገውን የታክስ መጠን፤እና

መ) ታክስ ከፋዩ ውሳኔውን ለመቃወም ወይም ይግባኝ ለማቅረብ ያለውን መብት፡፡

**100. Effect of Revision of a Tax Assessment Notice**

1/ A revised assessment issued under this Proclamation shall:

a) replace the original assessment to the extent of the revision; and

b) be deemed to be an assessment made under this Proclamation.

2/ Where the request for revision submitted by the taxpayer is rejected, the limitation period for lodging an objection under this Proclamation shall be computed from the date the initial assessment notice was served.

**101. Notice of Revised Assessment**

The Tax Authority shall serve a written notice of the revised assessment on the taxpayer specifying:

a) the nature of the error;

b) the reasons for the revision;

c) the revised amount of tax payable or refundable; and

d) the taxpayer’s right to objection or appeal.

**፩፻፪. <u>በተደጋጋሚ ማስተካከያ በማድረግ ላይ የተጣለ ገደብ</u>**

ማናቸውም የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በአንድ አይነት ስህተት ምክንያት ከአንድ ጊዜ በላይ ማስተካከያ ሊደረግበት አይችልም፡፡

፲፫) የአዋጁ አንቀጽ ፹፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፩፻፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፩፻፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

፩/ ይግባኝ በሚባልት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚፈልግ ሰው የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በሰላሳ (፴) ተከታታይ ቀናት ውስጥ የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም በውሳኔው ላይ ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይችላል፡፡

፲፬) የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፪ ንዑስ አንቀጽ (፮) ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፩፻፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፮) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፯) ተጨምሯል፡-

፯/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ላይ የተመላከተውን ሳያካትት በፊደል ተራ (ሀ) መሰረት ታክስ ከፋዩ በታክስ እዳው ላይ ከፍተኛ ጫናን የሚያስከትል አዲስ ማስረጃ ያቀረበ ከሆነ በታክስ ሕጉ መሠረት ሰነዱ በታክስ አወሳሰን ወቅት አስቀድሞ ባለመቅረቡ ምክንያት ሊከፈል ይገባ የነበረውን የታክስ ዕዳ ፲% (አስር በመቶ) ቅጣት ይከፍላል፡፡

**102. <u>Limitation on Double Revision</u>**

No tax assessment notice shall be amended more than once on the account of the same error.

13) Sub Article (1) of Article 88 or renumbered Sub Article (1) of Article 105 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 105 Sub Article (1):

1/ A person may appeal an appealable decision by filing a notice of appeal against the decision with the Commission in the approved form and within consecutive 30 (thirty) days of service of notice of decision.

14) A new Sub-Article (7) is added following Sub-Article (6) of Article 102 of the Proclamation or Sub-Article (6) of the renumbered Article 119:

7/ Without prejudice to the provisions under paragraphs (b) and (c) of Article 59 Sub-Article (3) of this proclamation ,Where a taxpayer presents new evidence pursuant to Article 59 Sub-Article (3) paragraph (a) of this Proclamation which would cause a significant hardship on their tax liability, the taxpayer shall, in accordance with the tax law, be liable to a penalty of 10% (ten percent) of the tax liability that ought to have been paid had the document not been previously withheld during the tax assessment.”

Habtamu Hailemeskel-Attorney & Legal Consultant

፲፭) የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፮ (፪) ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፩፻፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፡-

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ለድርጅት ወይም ለመንግሥት መስሪያ ቤት ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፣ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ከሚጣለው ቅጣት በተጨማሪ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፣ የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ፣ ዋና የሂሳብ ሹም ወይም ታክስ ተቀንሶ መያዝ እንዳለበትና የተያዘውም ታክስ መከፈል እንዳለበት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ማንኛውም ሌላ የድርጅቱ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የታክስ ባለስልጣኑ ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት ታክሱ ተቀንሶ ገቢ ያለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ እያንዳንዳቸው ብር ፪ ሺህ (ሁለት ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላሉ፡፡

፲፮) የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፰ ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፩፻፳፭ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፩፻፳፭ ተተክቷል፡-

**፩፻፳፭. የታክስ ደረሰኝ ያለመስጠት**

፩/ ደረሰኝ ሊሰጥ ሲገባ ያልሰጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለገዢ ባልሰጠው በእያንዳንዱ ደረሰኝ ብዛት ብር ፩ መቶ ሺህ ብር (አንድ መቶ ሺህ ብር) ቅጣት ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጣለው ቅጣት በባለስልጣኑ ሊነሳ አይችልም፡፡

15) Sub-Article (2) of Article 106 of the Proclamation or Sub-Article (2) of the renumbered Article 123 is hereby repealed and replaced by the following new sub-Article (2):

2/ Where Sub-Article (1) of this Article applies to a body or a public office, in addition to the penalty imposed pursuant to the same Sub-Article, the manager of the body, the head of the public office, the chief accountant, or any other employee of the body or public office who is responsible for ensuring that tax is withheld and paid, shall each be liable to a penalty of ETB 2,000.00 (Two Thousand Birr), provided it is established that the tax was not withheld and remitted prior to the tax Authority's request.

16) Article 108 of the Proclamation or the renumbered Article 125 is hereby repealed and replaced by the following new Article 125:

**125. Failure to Issue Tax Invoice**

1/ Any taxpayer who fails to issue a tax invoice when required to do so shall be liable to a penalty of ETB 100,000.00 (One Hundred Thousand Birr) for each invoice not issued to a buyer.

2/ The penalty imposed under Sub-Article (1) of this Article shall not be waived by the Authority.

፲፯) የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፳ ንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፩፻፴፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፣ በተጨማሪም ከንዑስ አንቀጽ (፯) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፰) ተካቷል፡-

፪/ ለአንድ ግብይት በተሰጠ ተመሳሳይ ደረሰኝ ላይ የተለያዩ ዋጋዎችን በመመዝገብ የሽያጭ ዋጋን ያሳነሰ ወይም የሽያጭ ዋጋን በማሳነስ ደረሰኝ የሰጠ ማንኛውም ሰው ብር ፩ መቶ ሺህ ብር (አንድ መቶ ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጫ እና ከአምስት እስከ ሰባት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፰/ ማናቸውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፴፩ (፩) ፊደልተራ (ለ) መሰረት ደረሰኝ ባለመስጠት ወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው የወንጀሉ ድርጊት የተፈጸመው በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ ለሁለት ጊዜያት ያህል አስተዳደራዊ ቅጣት ከተቀጣ በኋላ በሚሆንበት ጊዜ ነው።

፲፰) የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፴፪ ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፩፻፵፱ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፩፻፵፱ ተተክቷል።

**፩፻፵፱. <u>በድርጅቶች የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>**

፩/ የታክስ ህግን በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመው ድርጅት ወይም የሕግ ሰውነት የተሰጠው በግለሰብ ባለቤትነት ሥር ያለ የንግድ ሥራ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ በተፈጸመበት ወቅት የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ፣ የፋይናንስ ኃላፊ ወይም በተመሳሳይ

17) Sub-Article (2) of Article 120 of the Proclamation or Sub-Article (2) of the renumbered Article 137 is hereby repealed and replaced by the following new Sub-Article (2), and a new Sub-Article (8) is added following Sub-Article (7):

2/ Any person who understates the sales price by recording different prices on identical invoices issued for a single transaction, or who issues an invoice understating the sales price, shall be punishable with a fine of ETB 100,000.00 (One Hundred Thousand Birr) and rigorous imprisonment from five to seven years.

8/ Any person shall be held criminally liable for the offence of failure to issue an invoice under Sub-Article (1) of this Article and as per Article 131 Sub-Article (1) paragraph (b) of this proclamation only where the criminal act is committed after the person has been administratively penalized twice for the same act within a single tax period.

18) Article 132 of the Proclamation or the renumbered Article 149 is hereby repealed and replaced by the following new Article 149:

**149. <u>Offences Committed by Bodies</u>**

1/ Where an offence under the tax law is committed by a body or a business operated under sole proprietorship, the manager, financial head, or any person acting in a similar capacity at the time offense was committed shall be

የኃላፊነት ቦታ ላይ ያለ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን ማስረዳት ካልቻለ ወንጀሉን እንደፈጸመ ይቆጠራል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ስራ አስኪያጁ፣ የፋይናንስ ኃላፊው ወይም በተመሳሳይ የኃላፊነት ቦታ ላይ ያለው ሰው የሚከተሉትን ያስረዳ እንደሆነ በወንጀሉ ተጠያቂ አይሆንም፦

ሀ) ወንጀሉ የተፈጸመው ከርሱ እውቅና ውጪ መሆኑን፤

ለ) ወንጀሉ እንዲፈጸም ያልፈቀደ፣ ያላዘዘ ወይም ያልተባበረ መሆኑን፤ ወይም

ሐ) የዚህ አይነቱ ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል የሚያስችል የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት የዘረጋ መሆኑን።

፲፱/ ከአዋጁ አንቀጽ ፩፻፴፯ ንዑስ አንቀጽ (፬) ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፩፻፶፬ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል፦

፭/ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን በፊት ይግባኝ አቅርቦ በክርክር ላይ ያለ ታክስ ከፋይ የታክስ አለመግባባቱን በመስማማት ለመጨረስ የሚፈልግ ከሆነ ይህንኑ በመግለጽ አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በ፷ (ስልሳ) ቀናት ጊዜ ውስጥ ለታክስ ባለስልጣኑ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል።

deemed to have committed the offence unless such person can prove otherwise as provided under Sub-Article (2) of this Article.

**2/** Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the manager, financial head or person acting in a similar capacity shall not be held criminally liable if they prove that:

a) The offence was committed without his knowledge;

b) He did not permit, order, or connive in the commission of the offense; or

c) He had established an internal control system capable of preventing the commission of such an offense.

19) A new Sub-Article (5) is added following Sub-Article (4) of Article 137 of the Proclamation or Sub-Article (4) of the renumbered Article 154:

5/ A taxpayer who has filed an appeal and has a pending dispute prior to the effective date of this Proclamation may if they desire to resolve the tax dispute through conciliation, submit an application to the tax Authority to that effect within 60 (Sixty) days from the effective date of the proclamation.

፳) ከአንቀጽ ፷፩ ጀምሮ እስከ አንቀጽ ፩፻፴፱ ድረስ ያሉት የነባሩ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፸፪ እስከ አንቀጽ ፩፻፶፮ በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

፳፩) ይህ አዋጅ ከሚጸናበት ቀን በፊት ተጀምረው ፍጻሜ ያላገኙ ጉዳዮች በነባሩ አዋጅ መሰረት ፍጻሜ ያገኛሉ፡፡

**፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

20) The provisions of the existing Proclamation from Article 61 to Article 139 are hereby renumbered sequentially as Article 72 to Article 156.

21) Pending cases started before the issuance of this Proclamation shall be settled based on the provisions of the amended Proclamation.

**3. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 30th day of July 2026**

**TAYE ATSKESELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**